# ዘንድሮ

*ዘንድሮ፣ዘንድሮ፣ዘንድሮ*

***የሥንቱ ተወርቶ የሥንቱ ተነገር።***

***ዘንድሮ!***

***ወሎ በማደሩ ተዋሀደንና***

***መጥፎ ከደህና ጋር ተማታብንና***

***ብዙ ዓመታት አልፈው ዛሬ ነቃንና***

***ያስቀን ጀመረ ግራ ገባንና።***

***አዝማች***

***በዛኛው ተገርመን ጥቂት ሳንቆይ***

***የዚህኛው መባስ አያስቅም ወይ***

***ይህ ሁሉ ነገር ሥነት ዘመን ኖሮ***

***በጣም ያስገርማል ጉዳየን ዘንድሮ።***

***አዝማች***

***ብዙ ዓመት በድብቅ ሲጎዝ ከረመና***

***ዘንድሮ ላይ ሲደርስ ሸክሙ አጋደለና***

***ተዘክርኮ ወድቆ በግልፅ ብናየው***

***የዘንድሮን ነገር ዘንድሮ አየነው።***

## ***<u>የኳሥ አበደች ፖለቲካችን ማክተሜያ፤ የዘንድሮም መጨረሻ ናፈቀኝ</u>***

## ***<u>(ሰው ኢትዮጵያ)</u>***

*የጥላሁን ገሠሠ ምርጥ የሥልሳዎቹ ዘፈን ፖለቲካዊ አንድምታ አለው።*

*ዛሬ ላይ ሆኜ የጥላሁንን ዘፈን ስሰማ በአሁኑ ወቀት ያለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትኩሳት እጅግ በጣም የሳሰበኛል፡፡ትኩሳት የበሽታ ምልክት ነው ::አንድ የታመመ ሰው በሙቀት መሳሪ መለኪያ የሰውነቱ ሙቀት የለካል፡፡ሙቀቱ ከ37 ዲገሪ ሴንቲ ግሬድ በላይ ከሆነ በሰውነቱ ውስጥ በምርመራ የሚደረስበት በሽታ እነዳለ ያመለክታል፡፡ በወቅቱ የትኩሳቱ መንሰኤ ተውቆ ህክምና ካለገኘም የህመምተኛው ህይወት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ  ይታወቃል፡፡እነደሁም የፖለቲካ ትኩሳት ከመደበኛ ልኩ በላይ እየሆነ ከሄደ አደጋው የከፋ ይሆናል፡፡*

*ፖለቲካው በእጅጉ እየጋለ ነው፡፡ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ ወደመደበኛ ሙቀቱ ልንመልሰው ካልቻልን ሌላ ሌላ የሥልሳና ሰባዎቹ እልቂት ይከተላል፡፡ወደመደበኛ ሙቀቱ በአስቸኳይ ተረባርበን ካልመለሰነው  በጣም በቅርቡ ከጅጅጋው የባሰ  ሰብዐዊና ቁሳዊ ጥፋትና ውድመት እንደሚከሰት መገመት ነብይ አያሰኝም፡፡*

*የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትኩሳት ከመደበኛው በላይ ሆኖል፤ማለት፣ፖለቲካችን ታሟል ማለት ነው፡፡ ፖለቲከው ታመመ ማለት የፖለቲከውን መዘውር የያዙት ፣ፖለቲካውን እንዴት ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው እነደሚመሩት ከቶም አልገባቸውም ማለት ነው፡፡ህመሙ ከአዲሱ የጠ/ ሚ የለውጥ ሃሰብ ጋር የኢሕአዴግ ቁንጮ አባላት ለመራመድ እንደልቻሉ አመላካች ነው፡፡እንደውም ለውጡን ከልተቀበላችሁ እና ለውጡን በመደገፍ በመሥቀል አደባባይ እና በባህርዳር የወጣውን ህዝብ ሥሜት ካልተረዳችሁ ፣እኔንም አልተረዳችሁኝምና እዚህ ላይ ቢበቃኝ ይሻላል ያሉ ይመሥለኛል፡፡ ክቡር ደ/ ር ጠ/ ሚ አብይ አህመድ፡፡ አላዋቂዎችን ከጠበብ መራቅ ነውና የገደላቸው አንዳንድ  የኢሕአዴግ ቁንጮ አመራሮች በዶ/ ሩ ጥበብ ከልተጠቀሙ አስቀድመው መከራን የሚቀምሱት እነሱና በነሱ ሰበብ ሀብት ያፈሩት ዘመዶቻቸው እንደሆኑ ከወዲሁ ቢገነዘቡት መልካም ነው፡፡ለብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ግን ሺ ቢታለብ የሚደርሰው ከገል ስባሪ አይዘልም፡፡*

*ፖለቲካውን ከሚያንፈራፍረው ሙቀት ለማዳን ከወዲያ ወዲህ ፣ከወዲህ ወዲያ ሲባጁ የከረሙት ትሁቱ እና አዛኙ ጠ/ሚኒስተራችን ፣በእጅጉ የሚስቆጫቸው ፣በሳቸው መሪነት፣በራሰቸው ልብ ውስጥ ተጀምሮ ወደብዙዎቻችን የተላለፈው እና የሰረፀው የየቅርታ ፣የአንድነትና የፍቅር ሃሰብ ፣ በአንዳንድ የፓርአቸው ቁነጮ አባላት አእምሮ ባለመስረጹና ዛሬም ከሆዳቸው በላይ ማሰብ ሥለተሳናቸው የለውጡን ሂደት በፈለጉት ፍጥነት ለማስቀጠል አልመቻላቸው ይመሥለኛል፡፡አንድአንድ የፓርቲያቸው ቁንጮ ዓባለት አእምሮም ክፉኛ በዘረኝነት በሽታ መታመሙን ህዝቡ እየተናገረ በዝምታ እንዲመለከቱ መደረጋቸውም ደስ አላሰኛቸውም፡፡የኢሕአዴግ ፖለቲካ ከዘረኝነት ህመምም ሙሉ ለሙሉ እሰካልተፈወሰ ጊዜ ድረስም ከኢሕአዴግ ጋራ ይቀጥላሉ ብዬ አለምንም፡፡ብሔር ማለት ህዝብ ማለት ነውና ሰው መሆንን እና ዜጋነትን ብቻ የሚጠይቅ አንድ ህብረ ብሔር ፓርቲም ከኢሕአዴግ ተገንጥለው ቢያቆቁሙ ግን ይህቺ ሀገር ወደተሻለ ዴሞክራሳ ሥርዓት ግንባታ ትሸጋገራለች፡፡*

*ቀድሞውን በጥለዛ በሚያምን ባበደ ፖለቲካ ፣የሰከነ እና ሳይንሳዊነት ያለው ፖለቲካን ማሥረፅ በእጅጉ እነደሚከብድ የታወቀ ነውና የለውጥ ሃሳባቸው የማይተገበር ከሆነ ከኢሕዴግ ጋር ምን ይሰራሉ።*

*(በተለይም ከ43 ዓመት በፊት መለስ እነዳስቀመጣቸው ካሉ የህልም አለም ሰዎች ጋር ሆኖ ለውጥን ዐውን ማድረግ ከባድ ነው።ዛሬም የትግራይን ህዝብ አግተው ፣ፈቅርና አንድነትን አጥብቆ የሚፈልገውን ህዝብ ለራሳቸው አላማ ልቡ በጥላቻ እነዲሞላ እያደረጉት ነው።ዛሬም በዘመነ መሳፍነት አገዛዝ ውስጥ ያለን እስኪመስለን ድረስ ሠለዘር፣ሠለገዢነት እና ሥለጥላቻ በመስበክ ሥልጣናቸውን ለማራዘም እየጣሩ ነው።ፈፅሞ በማያዋጣ በአጥፍቶ መጥፋት መንገድ...)*

*ቀድሞውንም ቢሆን ፖለቲካችን ጤነኛ አልነበረም። ፖለቲካችን የኳስ አበደች ፖለቲካ ነበር።ዛሬ ደ/ሩ ሰከን እንበል ፣ከዘረኛ አስተሳሰብና ሆዳምነት ተላቀን፣ተዋደንንና ተፋቀረን ፣ሁላችንም ለሁላችንም ብልጽግና እንልፋ፣እንጣርና እንጋር፧ለኔ፣ለኔ፣ማለት ይብቃ።ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የጋራ ብልፅግና እና ምቾት ሌት ተቀን እንስራ።ቂምና ቁርሾ ይብቃ።ይቅር ተባብለን እነደበለፀጉት ሀገሮች በጋራ እንኑር።በማለት ከደርግና ከኢሕአዴግ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ውጪ የሆነ አዲስ እና ከዚህ በፊት ያልተሞከረ ሳይንሳዊና ሰላማዊ ፖለቲካን ለማራመድ በመነሳታቸው ፣ያ የለመዱት ልዩ የሥጋ ጥቅምን የሚያጎናፅፋቸው የኳስ አበደች ፖለቲካ ሥለቀረባቸው ብቻ፣በጠ/ሚራችን ላይ ፊታቸውን ማዞራቸው አይደቀንም።ነገር ግን እነሱ ያልተገነዘቡት ወይንም የረሱት ሃቅ ምንጊዜም ታሪክ የሚሰራው ህዝብ መሆኑን ነው።የሀገራችን ታሪክ ይህንኑ ሃቅ ነው የሚመሰክርልን።*

*የቅርቡን ታሪካችንን ብንዳስስ እንኳን ፤ቀኃሥን የህዝብን ብሶት ተገን አድረጎ በመስከረም ሁለት 1967 ከዙፋናቸው በማውረድ ፣ ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ ያወረዳቸው ደርግ ነው። ደርግ፣በሚሊቴሪ የተዋቀረ ኮሚቴ እነደመሆኑ፣ሥልጣንን ለህዝብ እሥረክቤ እኔ ወደ መደበኛ ሥራዬ እመለሳለው ብሎ ሲያበቀ፤ድሉን ከህዝብ በመንጠቅ ራሱን ቀለም እየቀባባ መንግስት ሆኖ ቁጭ አለ። ኢትዮጵያን አስቀድማለሁ በማለት ፣ምሎ የተገዘተው ደርግ፣ በኢትዮጵያ ህዝብና አብዮት ሥም ወጣቶችን በፀጉራቸው ጎፈሬነት ብቻ ገደለ።አንድ የቀበሌ አብዮት ጠባቂ የፈለገውን ሰው በአብዮቱ ሥም እሥከመግደል ደረሰ። በጥረታቸው ሀብት ያፈሩት ሀብታቸው ጠላት ሆኖባቸው ያለምንም የፈርድ ሂደት በጅምላ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ። በዚሁ ለመከራም ሆነ ለደስታ ማብሰርያ በሚፈለገው ሚዲያ ፣የፍየል ወጠጤን እያዘፈነ ደርግ ገድሎ ፎከረ። በቀኃሥ ዘመን "ገድሎ የማይፈክረው ዓምለክ ያውቃል።" የሚለው ጥቂት የማይባለው የኢትዮጵያ ህዝብም ያለ ሃጥያታቸው የህዝብን አብዮት ምክንያት በማድረግ ብቻ ደርግ በጅምላ ሲፈጃቸው "ጎሽ !ደግ አደረገ !። "አለ።*

*ታሪክ እንደሚነግረን ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነው፣በሥሜት የመነዳትና የኳስ አበደች ፖለቲካ "ሀ "ብሎ የተጀመረው።*

*የህንን በሥሜት የታጀበ የኳስ አበደች ፖለቲካ ፣ልክ እንደደርግ ያለ ህዝብ ምርጫ፣ በጠመንጃ ፣ሥልጣኑን ከደርግ የተረከበው ኢሕአዴግም ቀጠለበት።ህዝብን በድጋፍ ሰልፍ በግድ እያሰለፈ ፣ህዝብ ከእርሱ ጋራ የሌለውን ከኔ ጋራ ነው አለ፡፤ከደርግ በከፋ መልኩ ፤ህዝብ፣ከህዝብ ጋር እነዲቃቃር አደረገ። ተከታታይነት ባለው፣ሚዲያውን በተቆጣጠረ ቅስቀሳ ፣ሰው ሰው መሆኑን እነዲረሳና ለቋንቋ እንጂ ለሰው ቁብ እንዳይኖረው ለማድረግም ቻለ፡፤። በቋንቋ ሥምም ጥቂቶች ብቻ የሚጠልዙት ኳሥ አዘጋጅቶ ፣ሁሉም በየክልሉ ኳሷን እነዲጠልዝ አንፃራዊ መብት ሰጠው።(ኳስዋን እነዳሻው የመጠለዝ መብት የነበረው ግን በሹፌሩ ወንበር ላይ የተቀመጠው ብቻ ነበር።)በየከተማው በብዛት የሚኖረው ሰው ግራ እስከሚጋባ ድረስ፣ሰው ሰው መሆኑ ቀርቶ ቋንቋ መሆኑ ተነገረው።ሳይወድ በግዱም እናትህን ትተህ አባትህን ጥራና የፖለቲካ ኳሱን ከሚጠልዙት ጋር ተቀላቀልና የድርሻህን ቦጭቅ ።በፓርቲ አባልነት ሥም እንደጆርጅ ኦርዌል የእንስሳት ጉባኤ አይንት ስልጣን ሰጥቼሃለሁ።ሁሉም እንስሳት እኩልናቸው አንዳንድ እነስሳት ግን ከሁሉም እንስሳት የበለጠ እኩል ናቸው ተባለ ።ተባለ።ተባለ።አቤት!አቤት!...*

*(ሥልጣንን በአዲስ አበባ መሥተዳድር ለመያዝ ግን ዘር አልተጠየቀም።ይህ ነው እንግዲህ የእብዶች ፖለቲካ)*

*ቋንቋ ከቻልክ እና የሚጠለዘውን ኳስ የያዘውን ፣የጫዋተውን መሪ፣እንደግል አዳኝህ ከተቀበልክ፣ዓለም በጎንህ ታልፋለች።በመሪዎቹ ተባለ። የተባለውም ሆነ።እናም ንፁህ ህሊና ሳይሆን ጤፍ ሚቆላ ምላስ ያለው ሁሉ፣ሰውነቱን ክዶ ለቋንቋ ፖለቲካ ሰገደ።የስግደቱ ብድራትም ወድያው ተከፈለው።አይናችንን ጨፍነን በምንገልፅበት ቅፅፈት እሱ ሚሊዮነር ሆነ።ልማታዊ ባለሃብት ተባለ። በቋንቋ መሰላል በኳስ አበደች ፖለቲካ በመበልጸጉም ወያኔ/ኢህዴግ/ ሺ ዓመት ንገስ በማለትም የዘወትር ፀሎቱን ሳያሰልስ ተያያዘው።...*

*ድንገት ግን፣ ኢሕአዴግ ኳስ ጥለዛህን አቁም የሚል ተውልድ ተከሰተ።ህዝብ ታሪክ ሰሪ ነውና በህዝብ እጅ ጥምዘዛ ወያኔ/ኢሕአዴግ ፣የኳስ አበደች ፖለቲካውን ለመቆም ተገደደ። ከኢህአዴግ ማህፀን የወጡ ጥለዛው እንዲቆም ጉልህ ሚና መጫወታቸው የ2010 ዓ/ም ተአምራዊ ክስተት ነው።(ይህ ፀሃፊ የደርግ ወታደር እንደዛ ቄጤማ መሆን እና የጠ/ሚ አብይ አህመድ(ዶ/ር) ሰላማዊ አብየት በእጅጉ ያስገርመዋል።)*

*በጥለዛው የከበሩ አባላቱ ኳሷ በጠ/ሚ አብይ ሥር ተረጋግታ መቀመጦን ፈፅሞ አለወደዱም።ዛሬም በህዝብ ውስጥ መሽገው፣ህዝብ ውሃ አሮበት እነሱ በውስኪ እየተራጬ ፣ህሊና ቢስ መሰላቸውን በሃሺሺ አሰታጥቀው ሁከትና ብጥብጥ እነዲፈጥር ፣ህይወትና*

*ንበረት እነዲያጠፋ ማሰማረት ጀመሩ።ድንገት የሀይማኖታቸው ምሶሶ በመናዱ መሸሸጊያ በማጣታቸው ግራ ተጋቡ። የኳስ አበደች ፖለቲካ እንዲህ በዋዛ ሊጠፋ አይችልም በማለትም የሥወር ውጊያቸውን ጀመሩ።*

*የኳስ አበደች ፖለቲካ ተመልሶ እንዲመጣ የሚፈልግ አስተዋይ ህሊና ያለው ዜጋ ግን አላገኙም። የዐይናችሁን ጨፋኑና እናሞኛችሁ በማለት ቢሰብኩም አልተሳካላቸውም።በሃገራችን እድገትና ብልጽግና መጥቶ ሁሉም ዜጋ ወደየትም የሀገሩ ክልል በመዘዋወር ሰርቶ የሚኖርበትን ሃብት የሚያፈራበትን ፣የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ሌባ ያልሆነ ህሊና ያለው ሁሉ ያምናል ።ማንም የነሱን አጥር አለወደደውም።*

*በቋንቋ ሰበብ ግን አጥር አጥረው በመቀመጥ፣ የእኛ ክልል የራሳችን ብቻ ነው፤የእናንተ ደግሞ የእናንተም የእኛም ነው ማለት ጀመሩ። "ትፈራርሳለች።እንበታተናለን።"የሚልም ነጠላ ዜማ አወጡ።በሌላው ክልል ውስጥ የሚኖርን የራሴ የሚሉትን ህዝብ ሃብትና ንብረት ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም አደጋ ውስጥ የሚጥል ሂትለራዊ አስተሳሰብን ያዘለ ዘፈንም መዝፈን ጀመሩ።እንወክለዋለን ያሉት ህዝብ ግን ፈፅሞ አልሰማቸውም።በዘረኛ ዲስኩራቸው ተዋደንንና ተከባበረን በፍቅር እየኖርን ካለንበት ህዘብ ጋር አታጣሉን አላቸው እንጂ።*

*በተለያዩ ክልሎች ቤተሰብ መስርቶ ሃብትና ንበረትም አፍርቶ የሚኖር ፣ከሁለት የቋንቋ ተናጋሪ የተወለደ፣ በወሬ እንጂ የአባቱንም ሆነ የእናቱን የትውልድ ሀገር የማያቅ በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋ ፣ በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የሰው ሰውነትን የማይቀበልና ለዜጎች ኢትዮጵያዊ የሚል መታወቅያ የማይሰጥ የቀድሞዋ ሮዴሼያ አይነት ፖለቲካን የሚራምድ ሥርዓትን ነፍሱ ትጠየፍ ነበርና ላይመለስ ቢሄድለት ደስ ይለው ነበር።*

*ግን፣ግን ህዝብን በሥሜት እያስጨፈሩ፣ለአንተው ብልፅግና ነው ዛሬም የምንታገለው የሚሉ፣የቋንቋ ግብብነታቸውን በመጠቀም ብቻ ፤በግፍና በዘረፋ ያገኙት ንብረት አልበቃ ብሏቸው ፣በቀን አንድግዜ እንኳን በመከራ የሚጎርሰውን፣የዘረፉትን ትርፍራፊ በመስጠት ፣በተንኮል ቅስቀሳ ሰውነቱን በማስረሳት በድህነቱ ላይ ተጨማሪ መከራ ሊያመጡበት የሚጥሩ በየትም ክልል እስካሉ ግዜ ድረስ፣ልክ እንደ አሜሪካም ሆነ ቻይና ሰው በሰውነቱ ብቻ የሚከበርበትን ፤በእውነትና በሃቅ ሰርቶ የሚከብርበትን እና የሚከበርበትን ሀገር በቀላሉ ለመገንባት ከቶም አይቻልም።*

*ምክንያቱም፣የደ/ር አብይን የተቀደሰ እና ሰው ሰው የሚሸት ራዕይ፣ብዙዎቹ የፖለቲካ ፓርቲ ተዋንያኖች(በኢሕአዴግም ሆነ በተፈካካሪነት የተሰለፉ) አውቀው ተኝተው ወይንም*

*ከህሊና እና ከሞራል ልዕልና ይልቅ ሆዳቸው እና ምቾት በልጦባቸው ሊሆን ይችላል፣ዛሬም ከ45 ዓመት በፊት የነበረን ለአሁኑ ሰውና ተውልድ የማይጠቅምና ከዓለም ወቅታዊ ፖለቲካ ጋር ፈፅሞ የማይሄድ ፖለቲካ ያራምዳሉና የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይም ሆነ የኔ መሰሎች ህልም ከንቱ ሆኖ እነዳይቀር እሰጋሉሁ።*

*"ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም " ይባላልና ዘንድሮ፣ በ2010 ዓ/ም መጨረሻ ካየነው በእንጊሊዘኛው ጉድ ከሚሰኝ ፣የሚበልጥ ጉድ ለመስማት እንደምንበቃ ተሰፋ በማደረግ፣ከእኛ ሀገር የጉድ ትርጉም ፈጣሪ ይሰውረን በማለት ፅሁፌን የጥላሁንን ዘንድሮ የተሰኘውን ዘፈን ፍልጋችሁ እንድታደምጡ፣በማሳሰብ እሰናበታችኋለሁ።*

*ነሐሴ 13/2010 ዓ/ም*